የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት /2012 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የቀረበውን የ2011 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶቹን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ተቋሙ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በተቋሙ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የተቋሙ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ሚዛን መከራ፣

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**የወጪ ሂሳብ፤**

1. በተቋሙ ስም ላልተመዘገበ የሞባይል ስልክ የአራት ወር ብር 3,199.39 የአገልግሎት ክፍያ ለኢትዮ ቴሌኮም ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
2. ያለዋጋ ማወዳደሪያ በቀጥታ ከአንድ አቅራቢ የተፈጸመ የጎማ ግዥ በብር 22,750.00 ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡
3. በ3 የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 22,269.84 ደጋፊ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
4. ለቤት ኪራይ ክፍያ ወጪ የሆነ ብር 2,205,000.00 የክፍያ ማስረጃው ዋናው ሳይቀርብ በፎቶ ኮፒ ማስረጃ ሂሳቡ በወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡
5. ከኦሮሚያ ቅ/ጽ/ቤት ዋና እንባ ጠባቂ ከወር ደመወዛቸው ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የህክምና መዋጮ ብር 1,608.00 ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

**በጀት፤**

6. የመደበኛ በጀት ብር 730,990.43 ከተፈቀደው በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የተቋሙ የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሣያሉ፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች**

7. በኦሮሚያ ቅ/ጽ/ቤት በ3 የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 1900.01 የሂሣብ መደቡን ሳይጠብቅ የተመዘገበ ወጪ ተገኝቷል፡፡
8. በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 62,389.07 የተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡
9. ለባለመብቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ብር 402,261.22 ተገኝቷል፡፡
10. በመመሪያው መሰረት ያልተከናወነ የበጀት ዝውውር በድምሩ ብር 292,876.00 ተገኝቷል፡፡

11. ተቋሙ የስልክ የፍጆታ ክፍያ ተመን ወይም ገደብ የሌለው መሆኑ፤

<u>**ሌሎች ጉዳዮች**</u>

12. **ንብረት፤**

- በቋሚ ንብረት ክፍል(መጋዘን) ውስጥ የደንብ ልብስና ጫማ ፡ አገልግሎት የሚሰጡ እና የተለያዩ ወንበሮች ፤ጠረጴዛዎች፤የውሃ ማጣሪያዎች፤ ፎቶኮፒ ማሽን ፤ ሼልፎች፤ ዴስክቶፕ እና ላፕቶፕ ኮምፒተሮች ሊወገዱ የሚገባቸውና እንዲወገዱም ምንም ጥረት ያልተደረገላቸው የተለያዩ እቃዎች እና አገልግሎት የሚሰጡ ቋሚ እቃዎች በአንድ ላይ ተደራርበው በአንድ ክፍል ውስጥ ለእይታ በማያመች መልኩ ተከማችተው ተገኝቷል፡፡
- ለቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

----------------------------------

9/6/12

አንድነት ብዙሰው

የፋይናንሻል ኦዲት ሥራ አስኪያጅ